በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማ ርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/፩፬2/18

ቀን 27/04/2018 ዓ/ም

ለአብክመ ግብርና ቢሮ

<u>ባህር ዳር፤</u>

ጉዳዩ፡ <u>መመሪያ ምዝገባን ይመለከታል</u>

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው በመላክ እንዲሁም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት የአብክመ ግብርና ቢሮ በቁጥር ግቢ/ምቢ/ሐ/86/19 በቀን 23/04/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኮንትራት ዘር አመራረትና አስተዳደር መመሪያ ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል፡፡

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 31/2018 ዓ.ም አድርጎ የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 29 ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ይስማው ዘመነ
የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት
የክልል ዐቃቤ ሕግ

<u>ግልባጭ</u>

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  <u>ፍትህ ቢሮ</u>

## መመሪያ ቁጥር 31/2018 ዓ/ም

# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኮንትራት ዘር አመራረትና አስተዳደር መመሪያ

የሰብልን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ወሳኝ የግብርና ግብዓት የሆነውን ዘር በአይነት፣ በወቅቱ፣ በጥራትና በበቂ መጠን አምርቶ ለተጠቃሚው ማቅረብ አስፈላጊ ጉዳይ በመሆኑ ዘር አምራች ድርጅቶች በራሳቸውና በሌሎች ግለሰቦች ይዞታ ላይ በኮንትራት ምርት አመራረት ስርዓት ዘር እያመረቱ ያቀርቡ ዘንድ ሊያሰራ የሚችል የህግ ማዕቀፍ መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር በፌደሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ተደርጎ የወጣው የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1289/2015 እና አዋጁን ተከትለው በግብርና ሚኒስቴር የወጡትን መመሪያዎች ባከበረ መልኩ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ማወጣት በማስፈለጉ፣

በዘር አስመራቹና በዘር አምራቹ መካከል የሚያዘው የውል ስምምነት ግልጽ፣ የሚያሰራና አስገዳጅ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፣ በዘር አምራችና አስመራች መካከል ሊኖር የሚችለውን የመነሻ ዘር አቅርቦት አስተማማኝ ለማድረግ፣ የኮንትራት ዘር አመራረት ስርዓትን በማጠናከር የዘር ግብይት ስጋትን ለመቀነስ እንዲቻል፣ የዘር ደረጃን መሠረት አድርጎ የተቀመጠውን የዘር መግዣ ዋጋ በማሻሻል ወቅቱን የጠበቀ ርክክብ እንዲፈጽም ማድረግ በማስፈለጉ፤ የአርሶ አደሩን ምርጥ ዘር የመጠቀም አቅም ለማሳደግ፣ አምራችና አስመራች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል፣ በኮንትራት ዘር አመራረትና አስተዳደር ሂደት ውስጥ ያሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን በተገቢውና በተደራጀ መንገድ ለመፍታትና በኮንትራት ዘር አመራረት ስርዓት እየተገኘ ያለውን ጥቅም ይበልጥ ለማሳደግና የተጠቃሚውን የዘር ፍላጎት ለማረጋገጥ አስቻይ የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (4) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ይህን መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኮንትራት ዘር አመራረትና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 31/2018 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "ዘር" ማለት ለዕፅዋት ማራባት የሚያገለግል እውነ ዘር፣ አኩራች፣ የተክል ቁርጥራጭ፣ ሥራ ሥር፣ ችግኝ፣ ሳየን፣ መሰረተ ግንድ ወይም ሌላ ዓይነት የተክል አካል ነው፤

2/ "መነሻ ዘር" ማለት የአንድን ዘር ደረጃ ለማምረት በምንጭነት የሚያገለግል ዘር ነው፤

3/ "የዘር ደረጃ" ማለት አራቢን፣ ቅድመ መስራችን፣ መስራችንና እስከ ሶስተኛው ትውልድ ያለውን የተመሰከረለት ዘርን የሚያካትት ነው፤

4/ "ድቃይ የሆኑ ሰብሎች" ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የተለያዩ እናትና አባት ዝርያዎችን በማዳቀል የሚገኝ ዘር ነው፤

5/ "ድቃይ ያልሆኑ ሰብሎች" ማለት በተፈጥሮ የሚዳቀልና የሚራባ የሰብል ዝርያ ሆኖ ከድቃይ ዘር በተለየ ሁኔታ ለመጪው ምርት ዘመን ደጋግሞ በዘርነት ለመጠቀም የሚያስችል ዘር ነው፤

6/ "የዘር ጥራት ደረጃ" ማለት በመስክ እና በላብራቶሪ የተፈቀደ የዘር ጥራት መጠን መለኪያ ነው፤

7/ "ኮንትራት ወይም ውል" ማለት አስመራችና አምራች እየተባሉ በሚጠሩ አካላት መካከል የተለያዩ የሰብል ዘሮችን ለማምረት የሚደረግ የውል ስምምነት ነው፤

8/ "ኩታ-ገጠም" ማለት የጋራ ድንበር ያላቸው ዘር የሚመረትባቸው ማሳዎች ናቸው፤

9/ "አምራች" ማለት አግባብነት ካለው ባለሥልጣን ዘር ለማምረት የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠው አካል ጋር ውል ይዞ ዘር የሚያመርት ነው፤

10/ "አስመራች" ማለት ዘር ለማስመረት ከአምራች ጋር ውል የሚገባ፣ የኢንቨስትመንትና የንግድ ፈቃድ ያለው ወይም የህብረት ስራ ማህበር ሆኖ አግባብነት ካለው ባለሥልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው አካል ነው፤

11/ "የዘር ዋጋ" ማለት በኮንትራት የውል ስምምነት መሠረት ለተመረተ ዘር የሚከፈል ገንዘብ ነው፤

12/ "የዘር ጥራት ቁጥጥር ኮሚቴ" ማለት ከዘር አምራች ማህበራት ወይም ከአርሶ አደሮች ቡድን አባላት መካከል የዘር ጥራትን ለማስጠበቅ የተደራጀ ኮሚቴ ነው፤

13/ "የውስጥ የዘር ጥራት ቁጥጥር" ማለት ዘር አምራችና አስመራች ያመረተውንና ያስመረተውን ዘር በመስክና በላቦራቶሪ ደረጃ በራሱ ባለሙያዎች አማካኝነት በዘር ጥራት መስፈርት መሠረት የሚደርገው ቁጥጥር ነው፤

14/ "ባለስልጣን" ማለት የአማራ ክልል ግብርና ጥራትና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤

15/ "የግብርና ግብዓት" ማለት የእፅዋት ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ላይም ውህድ፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካል፣ የእርሻ መገልገያ መሳሪያዎች፣ ሰውነት መከላከያ ትጥቅ፣ የላብራቶሪ ኬሚካሎችና ቁሳቁሶች ናቸው፤

16/ "ማህበረሰብ አቀፍ ዘር ብዜት" ዝርያዎችን በስፋት ለማስተዋወቅ ታስቦ በምርምር ወይም በፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች የሚካሄድ የዘር ማባዛት ተግባር ነው፤

17/ "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት አንድ ሰው ዘር ማስመረት፣ ማዘጋጀት፣ ማከፋፈል፣ መቸርቸር እና ራስ አገዝ የዘር ጥራት ማረጋገጥ አገልግሎት ላይ ለመሰማራት ሲፈልግ መስፈርት ማሟላቱ ሲረጋገጥ የሚሰጥ ማስረጃ ነው፤

18/ "የግለላ ርቀት" ማለት በሁለት ተመሳሳይ ዝርያዎች ወይም የዘር ደረጃዎች ማሳ መካከል ሊኖር የሚገባው ዝቅተኛ ርቀት ነው፤

19/ "አግባብ ያለው አካል" ማለት የክልሉ ግብርና ቢሮ ነው፤

20/ "ተዋዋይ ወገኖች" ማለት ውል ሰጭ እየተባለ የሚጠራው ዘር አስመራችና ውል ተቀባይ እየተባለ የሚጠራው ዘር አምራች ናቸው፤

21/ "ሶስተኛ ወገን" ማለት ከአምራችና አስመራች ውጭ ያሉ የጥራት ተቆጣጣሪዎች ወይም አግባብ ካለው አካል ለውሉ መፈጸም ድጋፍ አቅራቢዎችን ያጠቃልላል፤

22/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

1/ ይህ መመሪያ በአማራ ክልል ውስጥ በኮንትራት ዘር ማምረትና ማስመረት ላይ በተሰማሩ ማንኛውም ዘር አምራችና አስመራች አካላት ላይ እና በግብርና ምርምር፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች የሚከናወን የማህበረሰብ አቀፍ ዘር ብዜት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ቢኖርም መመሪያው ለምርምር፣ ስርፀትና አዳዲስ አሰራሮችን ለማስተዋወቅ በሰርቶ ማሳያ በሚመረት ዘር ላይ እና በግብርና ምርምር፣ በፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች በአይነት የሚቀርብ የሰብል ዘር አመራረት፣ ስርጭት፣ አሰባሰብ እና አጠቃቀም ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፤

3/ ይህ መመሪያ የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በሀገር አቀፍ ደረጃ ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ተደርገው የወጡ የፌደራል መንግስቱን ህጎች ተፈጻሚነት አያስቀርም፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

መመሪያው የኮንትራት ዘር አመራረትና አስተዳደር በጥብቅ ህግ እንዲመራ በማድረግ፣ በአምራችና በአስመራች መካከል የሚኖረውን የውል ስምምነት በማስጠበቅና አስገዳጅ እንዲሆን በማድረግ ዘር በወቅቱ፣ በጥራትና በሚፈለገው መጠን እንዲመረትና እንዲቀርብ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ አላማ አለው፡፡

# ክፍል ሁለት

## ስለ ውሉ መነሻ ሀሳብ አቀራረብ፣የውል ፎርም፣ ይዘትና አደራረግ

5. የውሉ መነሻ ሀሳብ አቀራረብና ድርድር

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ የኮንትራት ዘር አመራረት ውል የሚጀመረው አስመራቹ ወይም አምራቹ በሚያቀርበው የውል ሃሳብ መነሻነት ነው፤

2/ የከንትራ ዘር አመራረት ውል መነሻ ሃሳብ በጽሑፍ ወይም በቃል ይቀርባል፤

3/ የመነሻ ሃሳቡ የዝርያውን አይነት፣ የዘር ደረጃ፣የመነሻ ዘር አቅርቦት ሁኔታ፣ የዘር ማምረቻ መስፈርቶች፣ የተመረተ ዘር መረከቢያ ዋጋ፣ የአከፋፈል ሁኔታ፣ የዘር መጠንን፣ የጥራት ደረጃን፣ የጊዜ ገደብን፣የማስረከቢያ ቦታና የማከማቻ መጋዘን፣ የሚያስፈልግ ድጋፍ፣ የክትትልና ሌሎች የተዋዋዮች ውሳኔ ሊደግፉ የሚችሉ መረጃዎችን ይጨምራል፤

4/ በንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው ቢኖርም ማንኛውም መንግስታዊ ተቋም ወይም መንግስታዊ ያልሆነ የልማት ድርጅት የኮንትራት ዘር አመራረት ውልን አስመልክቶ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሃሳብ ማቅረብ ወይም ማመቻቸት ይችላል፤

5/ የውሉ ሃሳብ የቀረበለት ተዋዋይ ወገን የውሉን ሁኔታዎች በአግባቡ ለመረዳት በቂ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል፤

6/ በድርድሩ ሂደት ተዋዋይ ወገኖች በሶስተኛ ወገን እገዛ ሊደረግላቸው ይችላል፡፡

6. የውሉ ፎርም

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ የኮንትራት ዘር አመራረት ውል በማያሻማ ሁኔታ በጽሑፍ መደረግ አለበት፤

2/ የኮንትራት ዘር አመራረት ውል አስመራችና አምራች ተስማምተው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ሊያዘጋጁ ይችላሉ፤ሆኖም ውሉ ከተዘጋጀባቸው ቋንቋዎች መካከል አንዱ የክልሉ የስራ ቋንቋ መሆን አለበት፤ በተለያዩ ቋንቋዎች በተዘጋጁ ውሎች መካከል ልዩነት ሲከሰት ውሉ የተደረገበት ክልል የስራ ቋንቋ አስገዳጅ ይሆናል፤

3/ የኮንትራት ዘር አመራረት ውል ቢያንስ በሶስት ምስክሮች ፊት መፈረም አለበት፤ ከምስክሮች አንዱ አግባብ ያለው አካል ተወካይ ሊሆን ይገባል፤

4/ የኮንትራት ዘር አመራረት ውል በክልሉ ውሎችን ለመመዝገብ ስልጣን በተሰጠው አካል መመዝገብ አለበት፡፡

7. የውሉ ይዘት

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ የውል አድራጊዎች ስም፣ አድራሻና ውል የተደረገበት ቀን፤

2/ የውሉ አላማ፤

3/ ዘር ለማምረት ስምምነት የተደረሰባቸው የሰብል ዓይነቶች፣ ዝርያ፣የዘር ደረጃና የማሳ ስፋት፤

4/ ለዘር ማምረት የሚውል መነሻ ዘር እና ሌሎች ግብዓቶች ስለሚቀርቡበት ሁኔታ፤

5/ የአስመራች መብትና ግዴታ፤

6/ የአምራች መብትና ግዴታ፤

7/ የዘር ጥራት መስፈርት መመዘኛዎች፤

8/ የዘር ምርት ርክክብ የሚደረግበት ቦታ ጊዜና አጠቃላይ የርክክብ ሁኔታ፤

9/ የዘር መረከቢያ ወይም ማስረከቢያ ዋጋ አወሳሰን ሁኔታ፤

10/ የክፍያ ሁኔታ፤

11/ ስለሚወሰድ የቅጣት እርምጃ፤

12/ አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታ፤

13/ ከአቅም በላይ የሆነ ሃይል ሲያጋጥም መወሰድ ስላለባቸው ሁኔታዎች፤

14/ ውሉ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ፤

15/ የተዋዋይ ወገኖችና እማኞች ስም፣ፊርማና ቀን፤

16/ የውሉ አካል የሚሆኑ አባሪዎች በተገቢው መንገድ የተካተቱበት መሆን አለበት፡፡

8. ውል መዋዋልና መፈራረም

1/ ማንኛውም ዘር አምራችና አስመራች አካል በተዘጋጀው የውል ሰነድ ላይ ውል ሳይዝና ሳይፈራረም ወደ ዘር ማምረት ስራ መግባት የለበትም፤

2/ የኮንትራት ዘር ማምረት ውል በአስመራች ድርጅትና በእርሻ ባለሃብቶች በተናጠል ወይም በአስመራች ድርጅትና አርሶ አደሮችን በሚወክሉ የዘር ብዜት ማህበራት ወይም

በአስመራች ድርጅትና በአርሶ አደር ቡድን ተወካዮች ወይም በአስመራች ድርጅትና ዘር አምራች አርሶ አደርን በሚወክሉ በሁለገብ ህብረት ስራ ማህበራት ወይም በአስመራች ድርጅትና ሌላ አቻ አስመራች ድርጅት መካከል ሊፈረም ይችላል፤

3/ ውሉ የሚፈረመው ዘር አምራች አርሶ አደሮችን በሚወክሉ የዘር ብዜት ወይም ሁለገብ ማህበር ወይም የአርሶ አደሮች ቡድን ከሆነ በዘር ብዜት ስራው ላይ ተሳታፊ ለሆኑ ሁሉም አ/አደሮች ዉሉ ተነቦላቸውና ተወያይተውበት ሲስማሙ ብቻ የማህበራቸው ተወካይ ወይም የቡድናቸው ተወካይ እነሱን ወክሎ ከአስመራች ድርጅቱ ጋር ውል መፈረም አለበት፤

4/ በተመሳሳይ ሁኔታ ማህበሩ ወይም የአርሶ አደር ቡድኑ አባል አርሶ አደሮች ከማህበራቸው ወይም ቡድናቸው ጋር በሚዘጋጅ ፎርም ላይ የተናጠል ውል መፈራረምና ስምና ፊርማውን ከአስመራች ድርጅት ውል ጋር አባሪ ማድረግ አለባቸው፤

5/ የመዋዋልና መፈራረም ስራው ሲፈፀም ከሁለቱ ተዋዋዮች አንድ አንድ እማኝ የሚያቀርቡት እንደተጠበቀ ሆኖ ከወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ወይም ከቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ወይም ከወረዳ ህብረት ስራ ማህበር አንድ ሰው እማኞች ሆነው መፈረም አለባቸው፤

6/ ውሉ በአራት ኮፒ ተሰርቶ ዋናው ለውል መዝጋቢ ተቋም፣ አንድ ኮፒ በአርሶ አደሩ ቡድን ተወካይ ወይም በማህበር አመራሮች፣ ሁለተኛው ኮፒ ለዘር አስመራች ድርጅት እና ሦስተኛው ኮፒ ደግሞ ከሙሉ ዝርዝር መረጃ ጋር ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የሚቀመጥ ሆኖ በዘር ማምርት የተሳተፉ አርሶ አደሮች ውሉን ከፈለጉ የውሉን ቅጅ ኮፒ አድርገው መያዝ ይችላሉ፤

7/ የዘር ማምረትና የማስመረት የውል ስምምነት ሂደት ከዘር ወቅት በፊት መፈፀም አለበት፤

8/ የዘር ግዥ የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት ወቅት በውል ሰነዱ ላይ እንደ ሰብሉ የመድረሻ ጊዜ ተጠቅሶ መቀመጥ አለበት፤

9/ በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላት በአምራችና አስመራች መካከል ውል እንዲያዝ፣ አምራች አርሶ አደሮች በውሉ ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ተዋዋይ ወገኖች ለውሉ ተገዥ እንዲሆኑ መስራት አለባቸው፡፡

# ክፍል ሶስት

## ስለአስመራቾች፣ ስለአምራቾችና ማምረቻ ቦታ መረጣ መስፈርቶች፣ ስለመነሻ ዘር አቅርቦት፣ ስለ ዘር ጥራት ሁኔታ፣ ስለ ዘር ዋጋ አወሳሰን እና ስለ ዘር ርክክብ

9. የኮንትራት ዘር አስመራቾች፣ አምራቾችና ማምረቻ ቦታ መረጣ መስፈርቶች

በኮንትራት ዘር አመራረት ሂደት ውስጥ ዘር የሚመረትባቸው አካባቢዎችና ተቋማት የዘር ማምረት ስራውን ውጤታማ ለማድረግ ወሳኝ በመሆናቸው ጥራቱ የተረጋገጠ ዘር በአይነት፣ በመጠንና በወቅቱ ለማምረት የሚከተሉት የማምረቻ መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ የዘር አስመራቾች መረጣ መስፈርቶች

ሀ) ማንኛውም ሰው በኮንትራት ዘር አመራረት ሂደት ዘር አስመራች ለመሆን የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 8(2) ከፊደል ሀ እስከ ሠ እንዲሁም በግብርና ሚኒስቴር የወጣውን የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት መመሪያ ቁጥር 1027/2017 አንቀጽ 10(1) ከፊደል ሀ እስከ ቀ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች፡-

1) ዘር ለማስመረት ፈቃደኝነት ያለው፤
2) በዘርፉ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ የሚችል ወይም የተመዘገበ ህብረት ስራ ማህበር ሲሆን፤
3) የግብርና ምርት ማስመረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያለው፤
4) በገለልተኛ ኦዲተር ኦዲት የተደረገ የአንድ አመት የሂሳብ ሪፖርት፤
5) የንግድ ዕቅድ አዘጋጅቶ ማቅረብ የሚችል፤
6) ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች የመስጠት አቅምና ፍላጎት ያለው፤
7) ግብዓት የማቅረብ አቅምና ፍላጎት ያለው፤
8) የመልካም አፈጻጸም ዋስትና የሚሆን ከአምራች ጋር ለማስመረትና ለመግዛት ከሚገባው ምርት መጠን ጠቅላላ የመገግዣ ዋጋ 2 በመቶ በዝግ አካውንት ማስያዝ፤
9) አስመራች በግለሰብ ደረጃ ከሆነ የጋብቻ ሁኔታ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ለ) ማንኛውም ሰው በኮንትራት ዘር አመራረት ሂደት በክልሉ ዘር አስመራች ለመሆን ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ማግኘት ያለበት ሆኖ፣ ሰርቲፊኬቱ የሚሰጠው የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ይሆናል፣

1) በባለስልጣኑ በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ መሰረት ለባለስልጣኑ ማመልከቻ ሲያቀርብ፣
2) በመስኩ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲኖረው፣
3) በመስኩ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ሲኖረው
4) በክልሉ ቢሮ ሲኖረው፣
5) የአንድ አመት በገለልተኛ ኦዲተር ኦዲት የተደረገ የሂሳብ ሪፖርት ሲያቀርብ፣
6) የንግድ ዕቅድ ማቅረብ የሚችል
7) ለህብረት ስራ ማህበራት ሲሆን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሲያቀርብ፣
8) የመልካም አፈጻጸም ዋስትና የሚሆን ከአምራች ጋር ለማስመረትና ለመግዛት ከሚገባው ምርት መጠን ጠቅላላ የመገግዣ ዋጋ 2 በመቶ በዝግ አካውንት ለማስያዙና
9) የቴክኒክ ድጋፍ የሚያደርግ ባለሙያ ያለው ለመሆኑ ማረጋገጫ ሲያቀርብ ይሆናል።

2/ የዘር ማምረቻ ወረዳዎችና ቀበሌዎች መረጣ መስፈርቶች

ሀ) ለኮንትራት ዘር አመራረት የሚመረጡ ወረዳዎችና ቀበሌዎች በተገቢው መንገድ የተጠኑና ለዘር ማምረት ስራ ሥነ-ምህዳራዊ ምቹነት ያላቸው መሆን አለባቸው፣

ለ) ለዘር ጥራት ቁጥጥር፣ ለክትትልና ድጋፍ፣ ለዘር ማጓጓዝና ትራንስፖርት አመችና ተደራሽ የሆኑና ዘር የሚመረትባቸዉ ማሳዎች በኩታ-ገጠም የተደራጁ መሆን አለባቸው፣

ሐ) ለዘር ማምረት የተመረጡ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ከኳራንቲን ተባዮች ነፃ ስለመሆናቸው በባለስልጣኑ የተረጋገጠ መሆን አለበት፣

መ) በዘር ማምረት የሚሳተፉ ወረዳዎች፣ ቀበሌዎችና ክላስተሮች በየደረጃው በሚገኙ የግብርና ተቋማትና ማህበራት ክትትልና ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፣

ሠ) በዘር ማምረት የተሰማሩ ድርጅቶች ዘር የሚመረትባቸውን ሰብሎችና ዝርያዎች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎችን ቀድመው ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፣

ረ) ለፋብሪካ የሚቀርብ የብቅል ገብስ ምርትና ለዘር የሚመረት የቢራ ገብስ በአንድ አካባቢ ወይም ቀበሌ መመረት የለባቸውም፤

ሰ) ዘር ማምረት በሚካሄድባቸው ቀበሌዎች በግብርና ምርምር፣ ማህበረሰብ አቀፍ ዘር ብዜት፣በፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ድጋፍ የሚቀርብ ዘር በተመሳሳይ ቦታ መግባት የለበትም።

3/ የአምራች አርሶ አደሮች ወይም ማህበራት መረጣ መስፈርቶች

ሀ) ለዘር ማምረት የተመረጠው ቀበሌ ዘር አምራች ማህበር ወይም የአርሶ አደሮች ቡድን ሊኖረው ይገባል፤

ለ) የዘር አምራች ማህበር ባልተቋቋመባቸው ቀበሌዎች ዘር አምራች ማህበር ወይም የአርሶ አደሮች ቡድን እስኪቋቋም ድረስ ሁለገብ የህብረት ስራ ማህበራት ውል ወስደው ሊሰሩ ይችላሉ፤ ሆኖም ግን በክላስተሩ ውስጥ አባል ያልሆኑ አርሶ አደሮች ሲኖሩ ከማህበሩ ጋር በመነጋገር ውል መያዝ አለባቸው፤

መ) ዘር አምራች አርሶ አደሮች በዘር ማምረት ስራ ላይ ከመሳተፋቸው በፊት በቂ ስልጠና ሊያገኙ ይገባል፤

ሠ) በዘር ማምረት የሚመለመሉ አርሶ አደሮች በውላቸው መሰረት ሙሉ በሙሉ ለዘር አስመራቹ ጥራቱን ጠብቀው ያመረቱትን ዘር ማስረከብ አለባቸው፤

4/ የማሳ መረጣ፣ የግለላ ርቀትና ልኬታ መስፈርቶች

ሀ) ለዘር ማምረት የሚውሉ ማሳዎች ለዘር ብዜት ምቹ የሆኑና ኩታ-ገጠም ሆነው የስፋት መጠናቸው፤ ድቃይ ላልሆኑ የጥራጥሬና ቅባት ሰብሎች ዝቅተኛው ከአምስት ሄክታር፣ለሌሎች ድቃይ ያልሆኑ ሰብሎች ከ10 ሄ/ርና ለድቃይ በቆሎ ከአርባ (40) ሄክታር በታች መሆን የለበትም፤

ለ) ከዘር ማምረት በፊት የዘር ብዜት የሚካሄድባቸው ማሳዎች ትክክለኛው የመሬት ልኬታ በጂፒኤስ መታወቅ አለበት፤

ሐ) ዘር የሚመረትባቸው የዘር ማሳዎች እንደየሰብሉ አይነት የተፈቀደውን ዝቅተኛ የግለላ ርቀት መስፈርት የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

10. የመነሻ ዘር አቅርቦት

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 13 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፦

1/ ዘር አምራች ድርጅቱ ለዘር ማምረት የሚያስፈልገውን የመነሻ ዘር ከሚመለከተው አካል ጋር አስቀድሞ ውል በመያዝ እንዲመረትለት ማድረግ አለበት፤

2/ የመነሻ ዘር በአስመራች ድርጅት እና በዘር አምራች አርሶ አደሩ በሚደረገው የውል ስምምነት መሰረት እጅ በእጅ ክፍያ ወይም በብድር ይቀርባል፤

3/ በክልሉና ከክልሉ ውጭ የሚቀርብ የመነሻ ዘር በዘር ህጉ መሰረት የጥራት ደረጃውን የጠበቀና የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን አለበት፤

4/ ከባለስልጣኑ በተለየ ሁኔታ ፈቃድ ካልተገኘ በስተቀር ከመስራች ዘር በታች የሆነ ዘር ለማባዣነት ጥቅም ላይ መዋል የለበትም፤

5/ በመደበኛ የዘር ማምረት ስራ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ድጋፍ በአይነት እየቀረበ የሚባዛ መነሻ ዘር ተቀባይነት አይኖረውም፤

6/ በኮንትራት ዘር አመራረትና አስተዳደር ወደ ዘር ማምረት ስራ የሚገቡ ዘር አስመራች ድርጅቶች መነሻ ዘር ለማግኘት ለምርት ዘመኑ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 11. የዘር ጥራት ሁኔታ

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 12 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ በኮንትራት ዘር አመራረት ዘዴ የሚመረትን ዘር እስከ ዘር ስርጭት ድረስ ጥራት የማስጠበቅ ስራ በሀገሪቱ በወጣው የዘር አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያና መስፈርት መሰረት በባለስልጣኑ ቁጥጥር ይደረጋል፤

2/ በሁሉም ዘር በሚመረትባቸው አካባቢዎች ኩታ-ገጠምን መሰረት በማድረግ ከዘር አምራች አርሶ አደሮች የተመረጡ የዘር ጥራት ቁጥጥር ኮሚቴ መዋቀር አለበት፤

3/ ዘር አስመራች ድርጅቶች የተጠናከረ የውስጥ ጥራት ቁጥጥር ማከናወን አለባቸው፤

4/ ከአርሶ አደሮች ዘር ጥራት ቁጥጥር ኮሚቴዎች በተጨማሪ የወረዳ ግብርና ጽህፈት ቤቶች ሌሎች ጥራትን የሚቆጣጠሩ አካላትን ሰይመው መከታተል አለባቸው፤

5/ የውስጥ ጥራት ቁጥጥር ኮሚቴው፣ የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት፣ የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤትና ህብረት ስራ ማህበር በየጊዜው የዘር አመራረት ሂደቱን መገምገም አለባቸው፡፡

## 12. የገበያ ጥናት እና የዋጋ አወሳሰን

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 10 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ በኮንትራት ዘር አመራረት የድቃይ በቆሎ የዘር ዋጋ በአስመራችና አምራች መካከል በሚደረግ የቀርጥ ዋጋ ስምምነት መሠረት የሚወሰን ይሆናል፤

2/ ከድቃይ በቆሎ ውጭ ባሉ ሰብሎች የዘር ዋጋ የሚወሰነዉ የአካባቢው የእህል ዋጋ ጥናት ተደርጎ በተገኘው ዋጋ ላይ ጭማሪ በማድረግ ይሆናል፡፡ ለዚህ ንዑስ ድንጋጌ አፈጻጸም፡-

ሀ) የአካባቢውን እህል የገበያ ዋጋ ለማጥናት ከወረዳ ግብርና ጽ/ቤት አንድ ባለሙያ፣ የህ/ሥ/ጽ/ቤት አንድ ባለሙያ፣ ከቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት አንድ ባለሙያ፣ ከዘር አስመራች ድርጅት አንድ ባለሙያ፣ ከዘር አምራች ሁለት አባላት እና ከወረዳው ንግድና ገበያ ልማት አንድ አባል በገበያ ጥናቱ ተወክለው በኮሚቴነት የሚሳተፉ ይሆናል፤

ለ) የወቅቱ የእህል ገበያ ጥናት የሚካሄደው አዲሱ የእህል ምርት ወደ ገበያ በሚቀርብበት ወቅት ይሆናል፤

3/ የገበያ ጥናቱ የሚካሄደዉ ዘር ብዜቱ በተካሄደበት ወረዳ ዋና ከተማ በሚገኝ ዋና የገበያ ቀንን ጠብቆ ነዉ፤

4/ ሆኖም ግን የገበያ ጥናቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተጠቀሰዉ አግባብ በተጠናዉ የገበያ ጥናት መግባባት ካልተቻለ የዘር ብዜት ባለተካሄደበት አጎራባች ወረዳ በሚገኝ ዋና ከተማ በሚገኝ ዋና የገበያ ቀን የእህል ዋጋ በማጥናት የሚወሰን ይሆናል፤

5/ አንዳንድ ሰብሎች ላይ ተመሳሳይ የምርት ናሙና በማይኖርበት አካባቢ እንደሁኔታው ከአካባቢው ገበያ ወጥቶ ሰብሉ በሚገኝበት አቅራቢያ መጠናት አለበት፤

6/ የአካባቢ የወቅቱ የእህል ዋጋ ከተጠና በኋላ የሚኖረው የዋጋ ጭማሪ ከተጠናው የአካባቢው የእህል ዋጋ ላይ ለተመሰከረለት ዘር 15 በመቶ እና ለቅድመ መስራችና መስራች ዘር ደግሞ 20 በመቶ በመጨመር ግዥ የሚፈጸም ይሆናል፤

## 13. የተመረተ ዘር ርክክብ

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 14 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ ዘር አስመራች ድርጅት ያስመረተውን ጥራቱን የጠበቀ ዘር ሙሉ በሙሉ የመረከብ፣ ዘር አምራች ደግሞ ያመረተውን ጥራቱን የጠበቀ ዘር ሙሉ በሙሉ የማስረከብ ግዴታ አለባቸው፤

2/ በኮንትራት ዘር አመራረት የተመረተን ዘር ግዥ ለመፈፀም በርክክብ ወቅት በባለስልጣኑና በውስጥ የዘር የጥራት ቁጥጥር ጥብቅ ክትትል ይደረጋል፤

3/ አስመራች ድርጅቶች የዘር ርክክብ ወቅትንና መረከቢያ ቦታዎችን ቀድመው ለአምራች አርሶ አደሮች ማሳወቅ አለባቸው፤

4/ ዘር አስመራች ድርጅቱ በዘር ግዥ ወቅት የሰው ሃይል፣ ልዩ ልዩ ቁሳቁስ እና መኪና መመደብና የግዥ ስርዓቱን የተቀላጠፈ ማድረግ አለበት፤

5/ በግዥ ወቅት የጥራት ስጋት ሲኖር የእርጥበትና የብቅለት ምርመራ ማከናወን ይገባል፤

6/ ለቀልጣፋ ርክክብና ጥራት ማስጠበቅ ይረዳ ዘንድ የዘር ውቂያ በተመረጡ እና ኩታ-ገጠም በሆኑ አውድማዎች በአንድ አካባቢ ብቻ ይሆናል፤

7/ የዘር ርክክብ አርሶ አደሩ ወደ መኖሪያ ቤት ሳይወስድ ከአውድማ ላይ ወይም በህብረት ስራ ማህበራት መጋዘን ላይ ብቻ ይሆናል፤

8/ ዘር አምራች አርሶ ደሮች የሚያስረክቡትን ዘር አስመራቹ በሰጣቸው ከረጢት ብቻ ተጠቅሞ ዘር ማቅረብ አለባቸው፤

9/ ባዕድ ነገሮችን ከዘር ጋር የሚቀላቅሉ አርሶ አደሮች አግባብ ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናሉ፤

10/ የዘር ርክክብ የምርት ግምትን እና የመረጃ ቋትን መሰረት አድርጎ መፈፀም አለበት፤

11/ በዘር ርክክብ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውል ሚዛን በተስማሚነት ምዘና ኢንስቲትዩት የተረጋገጠ መሆን አለበት፤

12/ በዘር ርክክብ ወቅት 100.5 ኪ/ግ በላይ የሆነ ዘር መዝኖ እንደ አንድ ኩንታል መረከብ አይቻልም፤

13/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰውን ባለማክበር ዘር አስመራች አስመርቶ ያልተረከበው ዘር ቢኖር ለአምራቾቹ በሚገቡት ውል መሰረት መክፈል ያለበትን ቅጣት እንዲከፍል ከተደረገ በኋላ ግብርና ቢሮ ዘሩ እንዳይባክን ሌሎች ህጋዊ ዘር አስመራች ድርጅቶች የዘሩን ዋጋ ለዘር አምራች ከፍለው እንዲረከቡት ሊያደርግ ይችላል።

## 14. የዘር ዋጋ ክፍያን በተመለከተ

1/ የግል ዘር አስመራች ድርጅቶች ከዘር አምራቾች በተረከቡት የዘር መጠን ልክ ዘሩ በመኪና እንደተጫነ ሳይንቀሳቀስ ክፍያዉን በባንክ መፈጸም አለባቸው፣

2/ ህብረት ስራ ማህበራት፣ ዩኒየኖችና የመንግስት ዘር አስመራች ድርጅቶች ዘሩን በተረከቡ እጅግ ቢዘገይ በ5 (አምስት) ቀናት ዉስጥ ክፍያዉን በባንክ መፈፀም አለባቸዉ፣

3/ ዘር ለሚያስረክቡ አርሶ አደሮች ማህበሩ ወይም የአርሶ አደር ቡድን ለተረከበው የዘር መጠን ማስረከቡን የሚገልፅ መተማመኛ ኩፖን መስጠት አለበት፤

4/ ክፍያ የሚፈጽሙ የፋይናንስ ተቋማትና ማህበራት ገንዘቡ እንደገባላቸው በፍጥነት ለአርሶ አደሩ ክፍያ መፈጸም አለባቸው፤

5/ አምራች አርሶ አደሮች የዘር ዋጋ ክፍያን በማህበራት አማካኝነት በሚቀበሉበት ወቅት በማህበሩ ከተቀመጠው መተዳደሪያ ደንብ ውጭ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍሉ መገደድ የለባቸውም፡፡

# ክፍል አምስት

## ስለክትትልና ድጋፍ፣አለመግባባቶችን ስለመፍታትና ከአቅም በላይ ስለሆኑ ምክንያቶች

### 15. ስለ ክትትልና ድጋፍ

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት መመሪያ ቁጥር 1027/2017 ከአንቀጽ 3 እስከ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ ዘር አስመራች ድርጅቶች ዘር አምራቾችን የግንዛቤ ፈጠራ ስራ፣ የአቅም ግንባታ ስራዎችንና ሙያዊ ድጋፎችን በተጠናከረ ሁኔታ መፈጸም አለባቸው፤

2/ ዘር አስመራች ድርጅቶች ለአምራች አርሶ አደሮች የግብርና ግብዓቶችን በወቅቱ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለባቸው፤

3/ ዘር አስመራች ድርጅቶች የዘር ስራን ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል በቂ ባለሙያዎችን መድቦ በተከታታይ ሙያዊ ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፤

4/ በዘር አስመራችና በአምራች መካከል በሚደረገው የዘር ማምረት ሂደት ውስጥ እንደ ሰብሉ ሁኔታ በየደረጃው ያሉ የግብርና ተቋማትና የህ/ስ/ማህበራት ባለሙያዎች ተከታታይ የሆነ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል ማድረግ አለባቸው፡፡

### 16. በውል አፈፃፀም ላይ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ሁኔታ

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 22 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዘር አስመራችና አምራች መካከል የተፈፀመ ውል ሳይጠናቀቅ አለመግባባቶች ቢፈጠሩ ፡-

1/ ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባቱን በራሳቸው ተወያይተው በድርድር መፍታት አለበቸው፤

2/ አለመግባባቱን በድርድር መፍታት ካልቻሉ አግባብነት ያለው አካል ወይም በሁለቱ ወገኖች በሚመረጥ ገለልተኛ ወገን በግልግል ዳኝነት ወይም ሽምግልና ሊስማሙ ይችላሉ፤

3/ አለመግባባቱ በግልግል ዳኝነት ወይም ሽምግልና መፈታት ያልቻለ እንደሆነ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ቀርቦ ወሳኔ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

17. ከአቅም በላይ ስለሆኑ ምክንያቶች

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ (17) የተደነገገው እና በግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት መመሪያ ቁጥር 1027/2017 አንቀጽ (9) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ በኮንትራት ዘር አመራረት ሂደት ውስጥ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች የሚባሉት የሚከተሉት ምክንያቶች ናቸው፡-

ሀ) ስራውን በቀጥታ ራሱ ከሚሰራው አምራች በኩል ፅኑ ህመም፤

ለ) ከመጠኑ ያለፈ ወይም ያነሰ ዝናብ፣ ጎርፍ፣በረዶ

ሐ) በጣም ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ሙቀት፤

መ) እሳት አደጋ፤

ሠ) የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም ናዳ ወይም የመሬት መንሸራተት፤

ረ) ከአምራች ግለሰቡ አቅም በላይ የሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ፤

ሰ) ከቁጥጥር በላይ የሆነ የእፅዋት በሽታና ነብሳት ተባይ ወረርሽኝ፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተዘረዘሩት ከአቅም በላይ የሆነ ሃይል ተብለው ሊወሰዱ የሚችሉት በውል በተጠቀሰው የዘር ምርት ላይ ያስከተሉት የጉዳት መጠን አምራቹ የገባውን ግዴታ በውሉ መሰረት መፈፀም የማያስችለው ስለመሆኑ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ወይም አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ እንደሆነ ነው፤

3/ የዘር ማምረት ውል ተዋዋይ ወገኖች በአስመራችና አምራች በኩል ከአቅም በላይ የሆነ ሃይል ሊባሉ የሚችሉ ክስተቶችን እና ውጤታቸውን በውላቸው ላይ ለይተው ሊያስቀምጡ ይችላሉ፤

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ወይም (2) በተገለፀው የዘር ማምረት ተዋዋይ ወገኖች ከአቅም በላይ የሆነ ሃይል በተፈጠረ ጊዜ አንዱ ለሌላው ወገን ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፤

5/ የዘር አመራረት ውሉን ለመፈፀም ከአቅም በላይ የሆነ ሃይል በተከሰተ ጊዜ ተዋዋይ ወገኖች የግብዓትና ሌሎች ወጭዎች አሸፋፈንን በተመለከተ በውላቸው ሊያካትቱ ይገባል፡፡

# ክፍል አራት

## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

18. የክልሉ ግብርና ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

1/ በዘር አስተባባሪ ኮሚቴና በዘር ቴክኒክ ኮሚቴ አማካኝነት የኮንትራት ዘር አመራረትን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤ ይመራል፤

2/ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ጉዳዩ በውይይት እንዲፈታ ጥረት ያደርጋል፤

3/ ዘር አስመራች ድርጅቶች ወቅቱን የጠበቀ የዘር ማምረት ውል መዋዋላቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ -----

4/ ክልላዊ የዘር ፍኖተ ካርታን ያዘጋጃል፣ ዘር አምራች ድርጅቶች መነሻ ዘር እንዲያመርቱ ያደረጋል፣የተመረተ መነሻ ዘር በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ይከታተላል፣

5/ የህግ ድጋፍ ያላቸው የውል ሰነዶች እንዲዘጋጁ ያስተባብራል ፤ይገመግማል፤ ይደግፋል፣

6/ በኮንትራት ዘር አመራረት ሂደት የሚመረት ዘር በምክረ- ሃሳቡ መሰረት እየተመረተ መሆኑን ይከታተላል፤ ይደግፋል፣

7/ ቢሮው በየደረጃው ለሚገኙ ዘር አስመራችና አምራች ድርጅቶች ሁለንተናዊ አቅም ይገነባል፣ የዘር ኤክስቴንሽን በተሟላ ሁኔታ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ ያስተባብራል።

19. የክልሉ ግብርና ጥራትና ቁጥጥር ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት

1/ በክልሉ ውስጥ ዘር ለሚያመርቱ አስመራቾች የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት አሰጣጥን በተመለከተ የፌደራል ግብርና ምርቶች አምራችና አስመራች ግንኙነት መወሰኛ ህጎችን እና ይህን መመሪያ መሰረት አድርጎ ተፈፃሚ ያደርጋል፤

2/ ዘር አስመራች ድርጅቶች በቂ፣ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ሃብት ሳይኖራቸው ወደ ዘርፉ እንዳይገቡ መስፈርት አውጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤

3/ የኮንትራት ዘር አመራረት ውጤታማ እንዲሆን ለዘር አምራችና አስመራቾች ሙያዊ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

4/ የዘር አስመራች ድርጅቶችን የውስጥ ጥራት ቁጥጥር አሰራርና የዘር አምራች ማህበራትን የውስጥ የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴዎችን ይደግፋል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

5/ የቀበሌ፣ወረዳና የዞን ግብርና እና ህብረት ስራ ማህበራት መዋቅር ድጋፍ ስለማድረጋቸው ይቆጣጠራል፤ ይደግፋል፣

6/ ከዘር በፊት፣ በዘር ወቅት፣ በሰብሉ እድገት ወቅት፣ በዘር ማሰባሰብና ርክክብ ወቅት በተቀመጠው የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት መሰረት ይቆጣጠራል፣ ይደግፋል፤

7/ የዘር አስመራች ባለሙያዎች፣ የቀበሌ የሰብል ልማት ባለሙያዎችና የአምራች ማህበራት የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴዎች በባለስልጣኑ የሚሰጡ ግብረ- መልሶች ስለመስተካከላቸው ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

8/ በኮንትራት ዘር አመራረት የተሰማሩ ለዘር አምራችና አስመራች አካላት ውል መያዛቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጣራል፤

9/ በኮንትራት ዘር አመራረት ሂደት የብቃት ጉድለት የታየባቸው ዘር አስመራች ድርጅቶችን የሰጣቸውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያግዳል፣ ይሰርዛል።

20. የክልሉ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ተግባርና ኃላፊነት

1/ የክልሉን የዘር ፍላጎት መሠረት ያደረገ መነሻ ዘር ለዘር አስመራቾች ለማቅረብ ውል ይዋዋላል፤

2/ በኮንትራት ዘር አመራረት በገባው ውል መሰረት በቂና ጥራቱን የጠበቀ መነሻ ዘር አምረቶ ያቀርባል፤

3/ አዳዲስ የሰብል ዝርያዎች ያፈልቃል፣ ያስለቅቃል የተለቀቀውን በሠርቶ ማሳያ የማስተዋወቅ ስራ በመስራት ለቀጣይ መነሻ ዘር እንዲመረት ያደርጋል፤

4/ በውሉ መሰረት የሚመረቱ መነሻ ዘሮች በተገቢው መንገድ ተዘጋጅተው፣ ታሽገውና የመለያ ምልክት ተደርጎባቸው ለአስመራቹ እንዲቀርቡ ያደርጋል።

21. የክልሉ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት

1/ ይህን መመሪያ ዘር አምራች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ተግባራዊ እንዲያደርጉት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሠራል፤

2/ ለዘር ማምረት በተመረጡ ቀበሌዎች ላይ የዘር አምራች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲደራጁ ያደርጋል፤

3/ የዘር አምራች የኅብረት ሥራ ማኅበራት በሚያወጡት የዘር አመራረትና ጥራት ቁጥጥር ህገ-ደንብ መሰረት ተግባራቸውን እያከናወኑ ስለመሆኑ ይከታተላል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤

4/ በየደረጃው ያለው ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይፈታል፤ የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፤

5/ የዘር አምራች የኅብረት ሥራ ማኅበራት የዘር ማከማቻ መጋዘን እንዲገነቡ ያደርጋል፣እገዛ ይሰጣል፤

6/ ስለ ዘር አመራረት፣መጋዘን አያያዝና የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አጠቃቀምን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላትና ሥራ አመራር አካላት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሠራል፤

7/ በተዋዋይ ወገኖች መካከል በሚደረገው ውል ላይ በተገቢው መንገድ ተግባብተው የተዋዋሉ መሆኑን በማረጋገጥ በእማኝነት ይፈርማል፣ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፡፡

22. ከዞን እስከ ቀበሌ ያለው የግብርና ቢሮ መዋቅር ተግባርና ኃላፊነት

1/ የዘር ማምረት አቅምን አስቀድሞ ይለያል፣ ጥያቄ ሲቀርብ ምላሽ ይሰጣል፤

2/ የኮንትራት ውሎች በተገቢው መንገድ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤ያስተባብራል፣በሚደረገው የውል ስምምነት ላይ በእማኝነት ይፈርማል፣ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤

3/ የዘር ማሳዎች በኩታ-ገጠም እንዲደራጁ ያደርጋል፣ የግለላ ርቀትን ያስጠብቃል፣ ከማሣ መረጣና ዝግጅት ጀምሮ እስከ ዘር ማሰባሰብ ወቅት ድረስ ለዘር አምራች አ/አደሮች አስፈላጊውን የኤክስቴንሽን የሙያ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ወቅቱን የጠበቀ የዘር የማሳ ልኬታ በጂ.ፒ.ኤስ ያከናወናል፤

4/ የውጭ የጥራት ቁጥጥር ሥራዎች ከመከናወናቸው በፊት ዘር አምራቾቹና አስመራቹ የውስጥ የጥራት ቁጥጥራቸውን እንዲያከናውኑ ድጋፍ ያደርጋል፤

5/ በዘር ርክክብ ወቅት የተጠናከረ ድጋፍ በማድረግ ርክክቡ ከአውድማ ወይም ከህብረት ስራ ማህበራት መጋዝን መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

23. የፋይናንስ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

1/ ከዘር አስመራች ድርጅቶች የክፍያ ትዕዛዝ እንደደረሰው በወቅቱ ለዘር አምራች እንዲከፈል ያደርጋል፤

2/ የዘር ዋጋ ክፍያን ለማሳለጥ እንዲቻል የዘር አምራች ማህበራትና አ/አደሮችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፍቱ ያደርጋል፤

3/ ለዘር አምራች ማህበራትና አስመራች ድርጅቶች ለመነሻ ዘርና ለግብዓት መግዣ የሚሆን ብድር ያመቻቻል፡፡

## 24. የዘር አስመራቾች ተግባርና ሃላፊነት

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 የተደነገገው እና በግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት መመሪያ ቁጥር 1027/2017 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ በኮንትራት ዘር አመራረት ተሳታፊ የሆኑ ማህበራትን በጥንቃቄ ይለያል፤

2/ ከዘር አምራች ማህበራት ጋር በተዘጋጀው የውል ስምምነት ሰነድ መሰረት ወቅቱን የጠበቀ ውል ይዋዋላል፤

3/ የዘር አመራረት ሂደት በምክረ ሃሰቡ መሰረት እንዲከናወን አምራች አርሶ አደሮችንና ስራውን የሚደግፉ ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፣ ይደግፋል፣ክትትል ያደርጋል፣ይቆጣጠራል፤

4/ ዘር የማምረት ሂደትን በተደራጀ መንገድ የውስጥ የጥራት ቁጥጥር ያከናውናል፤

5/ የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴዎችን ስራ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ያስተባበራል፣ይቆጣጠራል፤

6/ የዘር ኤክስቴንሽን ስርፀት ያሳልጣል፣ አዳዲስ ዝርያዎችን በሠርቶ ማሳያ በመስራት የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል፤

7/ ለዘር ማሰባሰብና ውቂያ የተመረጡ አውድማዎች በአንድ አካባቢ መሆናቸውንና የጥራት መጓደል የማያስከትሉ መሆኑን ያረጋግጣል፤

8/ በባለስልጣኑ በጥራት ቁጥጥር ያለፈውን ዘር ከአውድማ ላይ ወይም ማህበራት መጋዝን ላይ ብቻ ይረከባል፤

9/ በገባው ውል መሰረት ጥራቱን ጠብቆ የተመረተውን ዘር በወቅቱ ይረከባል፣ ለተረከበው ዘር በባንክ ወዲያውኑ ክፍያ ይፈጽማል፡፡

## 25. የዘር አምራቾች ተግባርና ኃላፊነት

የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1289/2015 አንቀጽ 9 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ ከዘር አስምራች ጋር በተዘጋጀው የውል ስምምነት ሰነድ መሰረት ወቅቱን የጠበቀ ውል ይፈጽማሉ፤

2/ ዘር አምራች አርሶ አደሮች ከማህበራት ወይም ከአርሶ አደር ቡድን መሪዎች ጋር በተዘጋጀው የውል ስምምነት ሰነድ መሰረት ወቅቱን የጠበቀ ውል ይፈጽማሉ፤

3/ የዘር አመራረት ሂደትን በምክረ-ሃሰቡ መሰረት ማለትም የግለላ ርቀት ማስጠበቅ፣ አደገኛ ተባይ፣አዘንባባ ማስወገድ፣ ነቀሳ፣ ወዘተ ያከናውናል፤

4/ የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴዎችን ይመርጣል፣ ኮሚቴዎች የሚሰጡትን አስተያየቶች ይተገብራል፣የውስጥ የዘር ጥራት ቁጥጥር ያካሂዳል፤

5/ ለዘር ማሰባሰብና ውቂያ የተመረጡ አውድማዎች በአንድ አካባቢ እንዲሆኑና የጥራት መጓደል የማያስከትሉ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

6/ በጥራት ቁጥጥር ያለፈውን ዘር ከአውድማ ላይ ወይም ማህበራት መጋዝን ላይ ብቻ ማስረከብ አለበት፤

7/ ዘር አምራች ማህበራት ለዘር አስመራቹ በውሉ መሠረት ለአስረከበው ዘር አስቀድሞ በተወሰነው ዋጋ ወይም በተጠናው የእህል ዋጋ መሠረት የዘር ዋጋን ከአስመራች ይቀበላል፣ ለአምራች አርሶ አደሮች ባስረከቡት የዘር መጠን ልክ ደግሞ ክፍያ ይፈጽማል፤

26. የአርሶ አደር የዘር ጥራት ቁጥጥር ኮሚቴዎች ተግባርና ኃላፊነት

1/ ዘር የሚመረትባቸው ማሳዎች በኩታ-ገጠም ወይም በኩታ-ገጠም መደራጀታቸውን ይቆጣጠራል፣ይደግፋል፤

2/ ምክረ-ሃሳቦችን በተለይ የአዘንባባ ማስወገድ፣ የነቀሳ እና ሌሎች ዋና ዋና የጥራት ማስጠበቅ ስራዎችን ያስተገብራል፣ ቁጥጥር ያደርጋል፤

3/ በክላስተሩ ውስጥ የማህበር አባል ያልሆኑ አርሶ አደሮች ሲኖሩ ከማህበሩ ጋር ውል እንዲገቡ ያደርጋል፤

4/ በግለሳ ርቀት ችግር ሲፈጠር ከአርሶ አደሩ ጋር ውይይት በማድረግ መፍትሄ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

5/ በምርት ግመታ ወቅት ከቀበሌ ባለሙያዎችና ከጥራት ተቆጣጣሪዎች ጋር በመሆን የምርት ግምቱን ይታዘባል፣ የራሱን የምርት ግምት ለጥራት ተቆጣጣሪው ያቀርባል፣

6/ በዘር ማሰባሰብና በውቂያ ወቅት አውድማዎች በአንድ አካባቢ እንዲሆኑ ያስተባብራል፣ይቆጣጠራል፤

7/ ዘር ከአውድማ ላይ ርክክብ ሲደረግ ወይም ወደ ማህበራት መጋዝን በሚገባበት ወቅት ባለስልጣኑ የሚሰጠውን መረጃና የምርት ግመታውን መሠረት አድርጎ ርክክብ መፈጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 27. የመመሪያው አካል ስለሆኑ አባሪዎች

በዚህ መመሪያ መጨረሻ አባሪ የተደረገው የኮንትራት ዘር አመራረት ውል ስምምነት ቅፅ የዚህ መመሪያ አካል ነው፡፡

### 28. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎችና አሰራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 29. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮው ፀድቆ፣ በክልሉ ፍትሕ ቢሮ ተመዝግቦ በአስተዳደር ተቋሙ ድረገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ባሕር ዳር

ቀን------ወር ------------/2018 ዓ/ም

የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ

# የኮንትራት ዘር አመራረት ውል ስምምነት ቅፅ

## የኮንትራት ዘር ማምረት ውል ስምምነት

### አንቀጽ 1

### ተዋዋይ ወገኖች

ይህ ውል ከዚህ በኋላ "አስመራች" ተብሎ በሚጠራው---------------------------------የሰርተፊኬት ቁጥር----------------------አድራሻ--------------------ከተማ---------------------ቀበሌ………… የስ/ቁ- --------------------------------- የፋክስ ቁጥር---------------------እና ከዚህ በኋላ "አምራች" ተብሎ በሚጠራው--------------------------------------አድራሻው --------------- ዞን ---------------- ወረዳ ……………ቀበሌ -------------- መካከል ዘር በማባዛት ለአስመራች በሽያጭ ለማቅረብ ወደን እና ፈቅደን የሚከተለውን የዘር ማባዛት ውል ተዋውለናል፡፡

### አንቀፅ 2

### ውሉ የሚመለከተው ጉዳይ

2.1. በዚህ ውል መሰረት አምራች ከዚህ በታች የተመለከተውን የሰብል ዘር ዓይነት በጥራት ተቆጣጣሪዎች በሚገመቱት መሠረት ዘር አምርቶ ለአስመራች በሽያጭ ለማቅረብ ተስማምቷል

| ሰብል | ዝርያ | የዘር ደረጃ | የማሳ ስፋት (ሄ/ር) |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |

### አንቀፅ 3

### የማባዣ ዘርና ሌሎች ግብዓቶችን ስለማቅረብ

3.1 የማባዣውን ዘር አስመራች ለአምራች በ------------------------ (በብድር፣እጅ በእጅ) ያቀርባል፣

3.2 የተመረተውን ያልተበጠረ ዘር መቋጠሪያ የሚሆን ጆንያ እና የመስፊያ ሲባጎ አስምራች ለአምራች ያቀርባል፡፡

3.3. ለዘር ማምረት አገልግሎት የሚውሉ ------------------------፣------------------------፣----------፣---- --------- ግብዓቶች በአስመራች ድርጅት በ------------------------ (በብድር፣ነፃ፣እጅ በእጅ) ይቀርባሉ፡፡

# አንቀፅ 4

## የተዋዋይ ወገኖች መብት እና ግዴታዎች

*4.1 የአስመራች መብቶች*

4.1.1 አስመራች በዚህ ውል በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የዘር ጥራት መስፈርቶችን ያሟላውን ዘር ብቻ የመረከብ መብት አለው፣

4.1.2 አስመራች በአምራች በኩል ተመርቶ የቀረበው ዘር የጥራት ደረጃው በውስጥ ላብራቶሪ ሲፈትሽ የሚገኘው ውጤት ካላረካው በጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን በኩል የማስመርመር መብት ይኖረዋል፣

4.1.3 የተመረተው ያልተበጠረ ዘር ተጓጉዞ እስከሚጠናቀቅ..................................ቀን ድረስ በአምራች መጋዝን የመጠቀም መብት አለው፣

4.1.4 የዘር ጥራት መስፈርቱን ያላሟላውን ዘር እንዲረከብ አይገደድም፡፡

*4.2 የአስመራች ግዴታ*

4.2.1 አስመራች በዚህ ውል መሰረት እንዲባዛ ለአምራች የሚያቀርበው የመነሻ ዘር የጥራት ደረጃ ያሟላና የጥራት ቁጥጥር ታግ ያለው መሆን አለበት፣

4.2.2 አስመራች ስለዘር አመራረት፣ አያያዝ እና ክምችት ለአምራች የሙያ ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

4.2.3 አስመራች በአምራቹ የተመረተውን ያልተበጠረ ምርጥ ዘር ከአውድማ ጀምሮ የጥራት ሁኔታው በባለሙያ ክትትል ተደርጎ ተቀባይነት ያገኘውን ዘር ከአምራች መጋዝን ድረስ በመገኘት ሙሉ በሙሉ የመረከብ ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም ግን የጥራት ጉድለት መኖሩን አስመራች በፊዚካል ወይም በላቦራቶሪ ካረጋገጠ አለመቀበል ይችላል፡፡

4.2.4 አስመራች በአምራች አማካኝነት እንዲመረት ያደረገውን ዘር የጥራት ደረጃውን ማሟላቱን በባለስልጣኑ ሲረጋገጥ ለዘር መቋጠሪያ የሚሆን ጆንያ እና የመስፊያ ሲባጎ ከአምራች ጥያቄ እንደደረሰው በ5 ቀናት ውስጥ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

4.2.5 አስመራች በአምራች በኩል የተመረተው ዘር እንዲነሳ በደብዳቤ በተገለፀለት በ5 ቀናት ውስጥ ዘሩን ተረክቦ አጓጉዞ ማንሳት ይኖርበታል፡፡

4.2.6 አስመራች የዘር ጥራት መስፈርቱን ያሟላውን ዘር ብቻ ከአምራች መጋዝን ድረስ በመገኘት ተረክቦ በራሱ ወጭ ያጓጉዛል፣

4.2.7 አስመራች የተመረተውን ዘር ተረክቦ እንዳጠናቀቀ በተረከበው ዘር መጠን ልክ የዘሩን ዋጋ በ----------------- (በእለቱ፣በ5 ቀን) ቀናት ውስጥ ለአምራች ክፍያ ይፈፅማል፣

*4.3 የአምራች መብቶች*

4.3.1 አምራች ያመረተውንና የጥራት መስፈርቱን ያሟላውን ዘር የማስረከብ መብት አለው፣

4.3.2. አምራች የጥራት ደረጃው የተረጋገጠለትን ዘር አጠናቆ እንዳስረከበ የዘሩን ጠቅላላ ዋጋ በ------------------ (በእለቱ፣በ5) ቀናት ውስጥ የማግኘት መብት አለው።

4.3.3 አስመራች በወቅቱ ምርቱን ባለማንሳቱ ምክንያት ለሚከሰት የዘር መበላሸት አስመራቹን በህግ የመጠየቅ መብት አለው።

*4.4 የአምራች ግዴታ*

4.4.1 ምርቱ ከመወቃቱ 15 ቀናት አስቀድሞ ጆንያ እና የመስፊያ ሲባጎ አስመራች እንዲያቀርብለት ይጠይቃል። የተላኩለትን ንብረቶች በጥንቃቄ በመያዝ ለተመረተው ዘር መቋጠሪያ ብቻ የማዋል ግዴታ አለበት።

4.4.2 ከላይ በንኡስ ቁጥር 4.4.1 መሰረት በተረከባቸው ጆንያዎች የተመረተውን ዘር ሰፍቶ ለአስመራች ያስረክባል። ከተመረተው ዘር በላይ የሚተርፉ ጆንያ እና ሲባጎ ቢኖር አምራች ለአስመራች የመመለስ ወይም በተገዛበት ዋጋ ሂሳብ የመክፈል ግዴታ አለበት፣

4.4.3 የተመረተው ዘር የጥራት መመዘኛዎችን የማያሟላ ከሆነ አስመራችን እንዲረከበው ማስገደድ አይችልም። ይህን ዘር ወደ ዘር ስርአቱ ቢያስገባ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

4.4.4. አምራች የዘር ጥራት መስፈርቱን አሟልቶ የተመረተውን ዘር የጆንያውን ክብደት ጨምሮ በ100.5 ኪሎ ግራም መዝኖና ሰፍቶ ለአስመራች የማስረከብ ግዴታ አለበት።

4.4.5. አምራች ያመረተውን ዘር ሙሉ በሙሉ የማስረከብ ግዴታ አለበት፣ቀንሶ በማስቀረት ለሌላ ወገን በዘርነትም ሆነ በሌላ መልክ አሳልፎ መስጠት አይችልም።

4.4.6. አምራች የሚያባዛውን ዘር ከሌላ ዘር ወይም በካይ ነገሮችን ሳይቀላቅል በጥንቃቄ አምርቶ ለአስመራች የማቅረብ ግዴታ አለበት።

4.4.7. አምራች በግድየለሽነት ወይም በአሰራር ችግር ወይም ሌላ ዘር በመቀላቀል ምክንያት ጥራቱ የተጓደለ ዘር ያቀረበ እንደሆነ አስመራች ዘሩን ለማስመረት ያወጣውን ወጪ የመክፈል ግዴታ አለበት፣

4.4.8. የተመረተው ዘር በመጋዘን ተከማችቶ ሲጠናቀቅ አምራች ለአስመራች ዘሩ እንዲነሳለት በእለቱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

4.4.9. አስመራች ዘሩን ተረክቦ በውሉ በተወሰነው ጊዜ ገደብ ውስጥ አጓጉዞ እስከሚያጠናቅቅ ድረስ ያለውን የመጋዘን ኪራይ እና የጥበቃ ወጭዎች በአምራች በኩል ይሸፈናል፣ ሆኖም ግን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ማንሳት ካልቻለ ወጪውን አስመራች ይሸፍናል።

4.4.10. የተባዛው ዘር ርክክብ በሚፈፀምበት ወቅት ወደ መኪና ለመጫን የሚያስፈልገው የጉልበት ሰራተኛ እና ከአውድማ ወደ መጋዝን ድረስ ለማጓጓዝ የሚያስፈልገውን ወጭ የሚሸፍነው አምራች ነው፡፡

4.4.11. ዘር አስመራቹ የዘር በዜት ማህበሩ ለሚያወጣቸው አንዳንድ ወጪዎች መሸፈኛና ማርጅን 120 ብር በአንድ ኩንታል ሂሳብ ኮሚሽን ይከፍላል፡፡

## አንቀፅ 5

## ስለዘር ጥራት እና ምርመራ

5.1 አምራች በውሉ መሰረት ያመረተውን ዘር ጥራትና ደረጃውን ጠብቆ የተመረተ መሆኑን በማረጋገጥ ለአስመራቹ ማስረከብ አለበት፣

5.2 አስመራች የዘር ጥራት ደረጃውን ከተጠራጠረ ናሙና በመውሰድ በላብራቶሪ ሊያስመረምር ይችላል፣

5.3 በንዑስ አንቀፅ 5.2 መሰረት በተደረገው ምርመራ ማረጋገጫ ውጤት መሰረት ዘሩ ተፈላጊውን የጥራት ደረጃ ያላሟላ መሆኑ ከተረጋገጠ አስመራች የተመረተውን ዘር እንዲረከብ አይገደድም፣

5.4 በአስመራች እና በአምራች መካከል ከዘር ጥራት ጉድለት ጋር ተያይዞ የሚነሳ አለመግባባት ቢኖር አግባብ ላለው አካል ናሙና በማቅረብ የላብራቶሪ ምርመራ ማካሄድ ይችላሉ፡፡

5.5 ከላይ በንኡስ አንቀፅ 6.4 መሰረት አምራች አምርቶ የሚያቀርበው ያልተበጠረ ዘር የጥራት ደረጃውን ያላሟላ መሆኑ በሚደረገው የጥራት ቁጥጥር ምርመራ ቢረጋገጥ ለምርመራው የወጣው ወጭ በአምራች ይሸፈናል፡፡

## አንቀፅ 6

## ስለዘር ዋጋ አወሳሰን እና የገበያ ጥናት ኮሚቴ አባላት

6.1 ከበቆሎ ውጭ የሚባዙ ዘሮች ዋጋ የሚወሰነው ከተለያዩ አካላት ተውጣጥቶ በወረዳ ደረጃ በተቋቋመ ኮሚቴ አማካኝነት በሚካሄድ የገበያ ጥናት የተመሰረተ ይሆናል፡፡ የዋጋ ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታም ዘሩ በተመረተበት አካባቢና በአቅራቢያ በሚገኘው ገበያ ላይ ይሆናል፡፡

6.2 የገበያ ጥናት ኮሚቴ አባላት በኮንትራት ዘር አመራረት መመሪያ ......./2018 አንቀፅ ....... (.....) በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፡፡

6.3 በኮሚቴው የተጠናው የገበያ ዋጋም ትክክለኛ እና የወረዳውን የገበያ ጥናት መረጃ መሰረት በማድረግ የተሰራ መሆኑን አስመራቹና አምራቹ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙትም በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት መሠረት እንደገና እንዲጠና ወይም የማሻሻያ ዋጋ ማቅረብ ይችላሉ፣

6.4 ከላይ በንዑስ አንቀፅ 6.3 በተጠቀሰው መሰረት ኮሚቴው ባጠናው የገበያ ዋጋ እና አስመራቹና አምራቹ ባቀረቡት የማሻሻያ ዋጋ መካከል ልዩነት ከተፈጠረ አስመራች እና አምራች ተደራድረው በመጨረሻ የሚስማሙበት የመግዣ ዋጋ ሆኖ አስመራች በደብዳቤ ሲያሳውቅ የዘር ግዥ ይፈፀማል፡፡

6.5 የዘር ዋጋ ለመወሰን እንዲቻል የሚቋቋሙ የገቢያ ጥናት ኮሚቴ አባላት ስብጥር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1ኛ/ ከወረዳው ግብርና ልማት ፅ/ቤት አንድ አባል ሰብሳቢ

2ኛ/ ከዘር አስመራች አንድ አባል ፀሐፊ ይሆናል

3ኛ/ ከቀበሌ ግብርና ፅ/ቤት አንድ አባል

4ኛ/ ከዘር አምራች ሁለት አባል

5ኛ/ ከወረዳው ንግድ እና ገበያ ልማት አንድ አባል

6ኛ/ ከወረዳው ህ/ሥ/ማ/ጽ/ቤት አንድ አባል ይሆናሉ፡፡

## አንቀፅ 7

## የተመረተ ዘር መረከቢያ ዋጋ

7.1 ዘር መረከቢያ/ማስረከቢያ የአንድ ኩንታል ዋጋ ከዚህ በታች እንደተመለከተው ይሆናል፡፡

7.1.2 የበቆሎ--------------ዝርያ ዘር ለአንድ ኩንታል ብር-------------/----------------------/ይሆናል፡፡

7.1.3 ከላይ በንኡስ አንቀፅ 7.1.2 ከበቆሎ ውጭ ለሚባዙ ሰብሎች በአካባቢው ገበያ ተጠንቶ በሚወሰነው ዋጋ ላይ ለተመሰከረለተ ዘር 15% እና ለቅደመ መስራችና መስራች ዘር 20% በመጨመር አስመራች ይከፍላል፡፡

## አንቀፅ 8

## የምርት ርክክብ ቦታ እና ጊዜ

8.1 አምራች ያመረተው ዘር ለርክክብ ማዘጋጀቱን ሲገልፅ አስመራች በተገለፀለት በ5 ቀናት ውስጥ ጥራቱን አረጋግጦ ማንሳት አለበት፡፡ ዘር አስመራች ከዘር አምራች ዘሩን አጠናቶ እስኪረከብ ድረስ ላነሳው ዘር ህጋዊ ደረሰኝ ወይም ኩፖን መስጠት ወይም ወዲያውኑ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፣

8.2 የዘሩ ርክክብ የሚፈፀመው ዘሩ በተመረተበት አካባቢ ከሚገኘው የማህበር መጋዘን ወይም አውድማ ይሆናል፣

8.3 አስመራች ዘሩን የሚረከበው እና አጠቃላይ የገንዘብ ክፍያ የሚፈፅመው ለተረከበው ዘር ብቻ ነው፣

8.4 አስመራች የጆንያውን ክብደት ጨምሮ የተመረተውን ዘር በ100.5 ኪ/ግ መዝኖ ከአምራች መጋዝን ይረከባል። አስመዝኖ ዘሩን ከተረከበ በኋላ ለሚደርሰው የሚዛን ጉድለት አምራች ተጠያቂ አይሆንም፤

8.6 አምራች እና አስመራች ከማህበራት መጋዘን ወይም አውድማ ላይ ርክክብ በሚደረግበት ወቅት የተመረተውን ዘር ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው ሰነድ ይረካከባሉ።

## አንቀፅ 9

## የክፍያ አፈፃፀም

9.1 አስመራች የተመረተውን ያልተበጠረ ዘር እንደተረከበ (በዕለቱ፣ በ5ቀናት) ገንዘቡን ለአምራች ይከፍላል። ክፍያውም በፋይናንስ ተቋማት በኩል ይሆናል፣

9.2. የዘር ዋጋ ክፍያውን ለመፈፀም የሚያስፈልገውን ወጭ የሚሸፍነው አስመራች ይሆናል።

9.3. አምራች ለተፈፀመለት ክፍያ ህጋዊ ደረሰኝ ለአስመራች ይሰጣል።

## አንቀፅ 10

## ገዥ ህጎች እና አለመግባባትን ስለመፍታት

10.1 ውሉን በተመለከተ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት አግባብነት ያላቸው ህጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

10.2 በዚህ ውል አፈፃፀም ላይ የሚነሱ ማናቸውም አለመግባባቶች በየደረጃው በሚገኙ የግብርና ተቋማት የማግባባት ስራ ይሰራል። ይህ ካልተቻለ ተዋዋዩቹ ጉዳያቸውን ስልጣን ላለው መደበኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ማስወሰን ይችላሉ።

## አንቀፅ 11

## ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት

11.1 በኮንትራት ዘር አመራረትና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር ---/2018 አንቀፅ 18 ስር የተጠቀሱት ስራውን በቀጥታ ራሱ ከሚሰራው አምራች በኩል ፅኑ ህመም፤ከመጠኑ ያለፈ ወይም ያነሰ ዝናብ፣ ጎርፍና በረዶ፤ በጣም ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ሙቀት፤ እሳት አደጋ፤ የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም ናዳ ወይም የመሬት መንሸራተት፤ ከአምራች ግለሰቡ አቅም በላይ የሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ እና ከቁጥጥር በላይ የሆነ የእፅዋት በሽታና ነብሳት ተባይ ወረርሽኝ ሲያጋጥሙ ችግር ያጋጠመው ወገን በውሉ አፈፃፀም አይገደድም።

11.2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 11.1 የተዘረዘሩት ከአቅም በላይ የሆነ ሃይል ተብለው ሊወሰዱ የሚችሉት የዘር ምርት ላይ ያስከተሉት የጉዳት መጠን አምራቹ የገባውን ግዴታ በውሉ

መሰረት መፈፀም የማያስችለው ስለመሆኑ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ወይም አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ እንደሆነ ነው፡፡

11.2 ከላይ በንዑስ አንቀፅ 11.1 መሰረት ከአቅም በላይ በሆነ ሃይል ውሉን መፈፀም ያልቻለው ተዋዋይ ወገን እጅግ ቢዘገይ በ5 ቀናት ውስጥ ለሌላው ወገን በፅሁፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

11.3 በአንቀፅ 11.2 ስር በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ የሆነ ሃይል መከሰቱን አንዱ ወገን በቅድሚያ ካላሳወቀ ከአቅም በላይ የሆነው ሃይል ተቀባይነት አይኖረውም፣ ከተጠያቂነትም አያድንም፡፡

## አንቀፅ 12

## ውሉ ፀንቱ የሚቀይበት ጊዜ

12.1 ይህ ውል ከተፈረመበት ዕለት አንስቶ አስመራች ዘሩን ሙሉ በሙሉ እስኪሚረከብበትና አምራች የዘሩን ዋጋ ሙሉ በሙሉ እስከሚቀበልበት ጊዜ ድረስ በሁሉም ወገኖች መካከል ፀንቶ ይቆያል፡፡

12.2 ሁሉም ወገኖች ይህንን ውል አንብበው በመረዳት በፈቃዳቸው ምስክሮች በተገኙበት ዛሬ ---------- ዓ.ም ከዚህ በታች በፊርማቸው በማረጋገጥ ውሉን ፈፅማዋል፡፡

| ስለአስመራች | ስለአምራች |
|---|---|
| ስም --------------------------- | ስም --------------------------- |
| ፊርማ ------------------------ | ፊርማ ............................... |
| ቀን -------------------------- | ቀን ---------------------------- |

12.3. ውሉ ሲፈፀም የነበሩ እማኞች

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| 1/ | ------------------------------------ | --------------------------- | ------------------------ |
| 2/ | ------------------------------------ | --------------------------- | ------------------------ |
| 3/ | ------------------------------------ | --------------------------- | ------------------------ |

## ዘር አምራች አርሶ አደሮች ከማህበራት ወይም የአርሶ አደር ቡድን ጋር ስለሚኖራቸው ውል

እኛ ከዚህ በታች ስማችን የተጠቀሰው ዘር አምራች አርሶ አደሮች ይህንን ውል ወደን እና ፈቅደን ተቀብለን በዚህ ውል መሰረት በጥራት ተቆጣጣሪዎች በሚገመተው መሠረት ሰብስበን በማህበራችን ወይም በቡድናችን በኩል ለአስመራች በሽያጭ ለማቅረብ በየስም አቅጣጫችን ፈርመናል፡፡

*ሠንጠረዥ ማህበራት ከአባላት ጋር የሚፈራረሙበት ቅጽ*

| ተ.ቁ | የአርሶ አደሩ ስም | የሚባዛው ሰብል ዓይነት | ዝርያ | ደረጃ | የማሳ ስፋት /ሄ/ር/ | ስምና ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |